የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 33
ADDIS ABABA, 9th July, 2024

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፯/፪ሺ፲፮

ለኢትዮጵያ ንግድ ሎጅስቲክስ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ…………… ……………………………………………ገጽ ፲፭ሺ፮፻፲፭

## Content

Proclamation No. 1317/2024

International Development Association Loan Agreement for Additional financing for the Trade Logistics Project Ratification Proclamation ……..……..…...... Page 15615

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፯/፪ሺ፲፮

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለኢትዮጵያ ንግድ ሎጅስቲክስ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ፷፰ሚሊዮን ፭፻ሺ (ስልሳ ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ.ሕ) ኤስ.ዲ.አር ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፲፯ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1317/2024

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to SDR 68,500,000 (Sixty-Eight Million Five Hundred Thousand SDR) Special Drawing Rights Additional financing for the Trade Logistics Project was signed in Addis Ababa on 24th day of January, 2024;

**WHEREAS**, the House of peoples' Represe ntatives of the Federal Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 14th day of March 2024;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby Proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ ንግድ ሎጅስቲክስ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፉ የልማት ማሕበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ፩ሺ፫፻፲፯/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Additional financing for the Trade Logistics Project Ratification Proclamation No. 1317/2024".

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማሕበር መካከል ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7464-ET በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement Number 7464-ET signed in Addis Ababa on 24th day of January, 2024 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## ፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፷፰ሚሊዮን ፭፻ሺ (ስልሳ ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺሕ) ኤስ.ዲ.አር. በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## 3. Power of the Ministry of Finance

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to SDR 68,500,000 (Sixty-Eight Million Five Hundred Thousand SDR) Special Drawing Rights in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

አዲስ አበባ ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

ሣህለ ወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**Done at Addis Ababa, On this 9th Day of July, 2024**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**